# አማራ ሆይ! እናት ደግን ዓለምም ደካማን አትወድም!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

አማራ ሆይ! “ከራሴ በፊት ለኢትዮጵያ እናቴ”ን እየዘመርክ ተወራሪ ጋር ተናንቀህ አጥንትህን የከሰከስክላትና ደምህን እንደ ጅረት ያፈሰስክላት እናትህ ለአለፉት አምሳ ዓመታት “ተው ቻለው ባንተ ይቅር ስትልህ” እሽ በማለትህ የደረሰበትን በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ መከራና ግፍ አይተኻል፡፡ የእናትህን ስም በከንቱ እያነሱ አንገትህን ቆርጠዋል፤ እሬሳህን መሬት ላይ ጎትተዋል፤ ተቤተክርስትያንህና ተመስጊድህ ውስጥ አቃጥለውሃል፡፡ ልጃገረዶችህን በመርዝ አምክነዋል፤ ወንዶቹን ተወህኒ ቤት ዘር እንዳያፈሩ አድርገዋል፡፡ ተማሪዎችህን ጠልፈው አጥፍተዋል፡፡ አያቶችህ ተመሰረቱትና ተጠበቁት አገር እያሰደዱ ሜዳ ላይ እንኳን መተኛት የማትችል ስትባረር የምትከርም ስደተኛም አድርገውሃል፡፡

አማራ ሆይ! ጨርሰው ሊያጠፉህ ሲፈለጉም አማራ ጨቋኙ ሲሉ እንዳልነበረ ሁሉ አሁን መልሰው “አማራ የለም!” ማለትም ጀምረዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ለወደፊቱ የታለመልህ ግፍ አማራን ጨርሶ እስከማጥፋትና አማራ አልነበረም እስከማለት የሚደርስ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ እናት ልጇና የልጅ ልጇ ተምድር እንዲጠፋ ስለማትፈቅድ ተምድር የሚያጠፋህ ጭራቅ ሲመጣ ለእናት ደግ መሆን እዚህ ላይ ያከትማል፡፡




የእናት ምክርን ሰምተህ መታገስህን አይታ የደከምክ የመሰላት ዓለምም የምትሰራህን አይተኻል፡፡ ከአገራት በፊት አገር መስርተህ፣ ጥበብን፣ ቅኔና ፍልስፍናን እንደ ምንጭ አፍልቀህ፣ ባህልን፣ ሥነ-ምግባርንና የመንፈስ ልእልናን እንደ ጥበብ ሸማ ጠብበህ፣ በአንድ አምላክ የተመሰረቱ ጥኑ ሃማኖቶችን በአለት ላይ ገንብተህ፣ ድንቅ የሆነ የቀን መቁጠሪያን ቀምመህ፣ ፍልስፍናን ቅኔን ሊያዳብር የሚችል ጊዜና ወረቀት የሚቆጥብ አቻ የሌለው ፊደል ፈጥረህ፣ የነፃነትና የሉአላዊነት ትርጉም በሚገባ ተረድተህ ወራሪን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ያስተማርካት ዓለም አመድ አፋሽ እንዳደረገችህ አይተኻል፡፡

አያቶችህን እንደ አንበሳ ትፈራ የነበረችው ዓለም ዛሬ ደካማ መስለህ ስለታየኻት ባህልህን ልታጠፋ በባህል እከክ እንደ ወረረችህ አይተኻል፡፡ ቋንቋህንና ፊደልህን ልታጠፋ በላቲን የእርሳስ ላፒስ እንደወረረችህ አይተኻል፡፡ ሃይማኖቶችህንም ልትበርዝ የማትፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ ተገንዝበኻል፡፡ የቀን መቁጠሪያ ቀመርህን ለማጥፋትም ቁማር በመቆመር ላይ መሆኑን መገንዘበ ይኖርብሃል፡፡ ምን ብትበደል በዳዩ አንተ እንደሆንክ ለምስክርነት ሳትጠራም እየመሰከረችብህ እንደሆነ አጢነኻል፡፡

አማራ ሆይ! እናት ጨፍጭፈው እስከሚጨርሱህና የመንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ሐብትህ እስከሚጠፋ ደግ ሁን ብላ እንደማታውቅ መገንዘብ ይገባኻል፡፡ ዓለም ድሮም፣ ዛሬም ሆነ ነገ ደካማ እንደማትወድ እንደ ቅድመ አያቶችህ በሚገባ ማጤን ይኖርብኻል፡፡ ስለዚህ አማራ ሆይ! ለእናት ደግ ለዓለምም ደከማ መስሎ መታየቱ አሁኑኑ ይበቃኻል፡፡ የደረሰብህንና የሚደርስብህን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚመለከተው አምላክ “እርዳኝ እረድኻለሁ!” በሚለው ቃሉ ለመኖርና ግፍን ለመከላከል በምታደርገው ትግል ይረዳኻል፡፡ አሜን፡፡

*ሚያዚያ ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ.ም.*